# የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት

# የቋሚ ሠራተኞች የመኖሪያ ቤት ድልድል፣ ማልገያ ዕቃዎች አሰጣጥና አጠቃቀም መመሪያ

መመሪያ ቁጥር፡ 817/2013

ሐምሌ 2007 ዓ.ም
አዲስ አበባ

# ማውጫ


| ርዕስ | | ገጽ |
|---|---|---|
| 1. | መግቢያ | 3 |
| 2. | የመመሪያው ዓላማ | 3 |
| 3. | ትርጓሜ | 4 |
| 4. | የመኖሪያ ቤት ድልድል መመዘኛ መስፈርቶች | 5 |
| 5. | የመኖሪያ ቤት ድልድል/ሽግሽግ አፈጻጸም ቅደም ተከተል | 5 |
| 6. | በሥራ ባህሪ ምክንያት መኖሪያ ቤት ያለ ወጪ የሚፈቀድላቸው ሠራተኞች | 6 |
| 7. | እንደሚከለሉ ሁኔታ በሚከለሉ ወስጥ ባሉ በደረጃ 3 እና በታች ቤቶች ወስጥ ያለ ወጪ እንዲኖሩ የተፈቀደላቸው | 6 |
| 8. | ተመራማሪወ/ባለሞያው ባለበት ደረጃ ላይ ባሉ ቤቶች ያለወጪ እንዲኖሩ የተፈቀደላቸው | 6 |
| 9. | ለተመራማሪዎችና ለድጋፍ ሰጭ ሠራተኞች የመኖሪያ ቤት ድልድል/ሽግሽግ መመዘኛ መስፈርቶች የመወዳደሪያ ነጥብ አሰጣጥ | 6 |
| 10. | የኢንስቲትዩቱን መኖሪያ ቤትና ማልገያ ዕቃዎች ድልድል/ሽግሽግ የማስተባበር ኃላፊነት | 8 |
| 11. | የማከል መኖሪያ ቤት ድልድል/ሽግሽግ ኮሚቴ ተጠሪነትና ኃላፊነት | 8 |
| 12. | በማከላት የኮሚቴ አባላት ዝርዝር | 8 |
| 13. | የመኖሪያ ቤትና የቤት ማልገያ ዕቃዎች ድልድል/ሽግሽግ አፈጻጸም፣ አያያዝና አጠቃቀም | 9 |
| 14. | የመኖሪያ ቤትና የቤት ማልገያ ዕቃዎችን በተመለከተ የሠራተኞች ግዴታ | 10 |
| 15. | የመኖሪያ ቤት አጠያየቅና አሰጣጥ ሂደት | 12 |
| 16. | ልዩ ልዩ | 15 |
| 17. | የመመሪያው ተፈጻሚነት | 15 |
| 18. | መመሪያውን ስለማሻሻል | 15 |
| 19. | የተሻሩ መመሪያዎች | 15 |

20. መመሪያው የሚፀናበት ____ 15

## 1. መግቢያ

የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የግብርናውን ክፍለ ኢኮኖሚ ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ ቴክኖሎጂ በማፍለቅ፣ በማላመድና በማስረጽ ረገድ ቀደም ሲል የደረሰበትን የላቀ የእድገት ደረጃ በማስጠበቅ ለተሻለ ስኬት በጽናት እየሠራ ነው፡፡ ኢንስቲትዩቱ የተመራማሪዎችን እውቀትና ክህሎት በተሻለ ብቃት ለመጠቀም ከሚያስገልባቸው ስልቶች አንዱ ለምርምሩ ሥራ ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር ተመራማሪዎች ምርምሩ በሚካሄድበት አካባቢ በቅርበት በመኖር የምርምሩን ሥራ በተረጋጋ ሁኔታ እንዲያከናውኑ የመኖሪያ ቤት በተገነባላቸው ማዕከላት የመኖሪያ ቤት አገልግሎት እንደተቋሙ ሠራተኛ ምድብ (ተመራማሪና ድጋፍ ሰጭ) ማቅረብ ነው፡፡

ኢንስቲትዩቱ ተመራማሪዎችን ለማበረታታትና ለማትጋት እንዲቻል ለኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ያቀረበው አዲስ የደመወዝ ማሻሻያና ጥቅማ ጥቅም ፓኬጅ በመንግሥት ጸድቆ ከግንቦት 1 ቀን 2006 ዓ.ም. ጀምሮ ሥራ ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡ ይህ የደመወዝ ማሻሻያና ጥቅማ ጥቅም ፓኬጅ መኖሪያ ቤት ላልተሰጣቸው የመኖሪያ ቤት አበልን የሚያካትት በመሆኑ ከነሐሴ 2004 ዓ.ም ጀምሮ በሥራ ላይ የነበረውን ካየመኖሪያ ቤትና ማልገያ ዕቃዎች ድልድልና አጠቃቀም መመሪያካ በአዲስ መልክ መከለስና ማሻሻል አስፈላጊ ሆኗል፡፡

## 2. የመመሪያው ዓላማ

ኢንስቲትዩቱ በአገር አቀፍ ደረጃ የተሰጠውን ከፍተኛ ኃላፊነት ለመወጣትና በምርምር ቀጣይነት ያለው ውጤት ለማምጣት እንዲቻል በርካታ ተመራማሪዎችን ቀጥሮ በማሠራት ላይ ይገኛል፡፡ እነዚህ የምርምር ሞያተኞች በሰከነ መንፈስና በተረጋጋ አእምሮ ቴክኖሎጂዎችን ለማፍለቅ፣ ለማላመድና ለማስረጽ እንዲችሉ ምቹ የሥራ አካባቢን መፍጠር አስፈላጊ ነው፡፡

በመሆኑም፡-

- ተመራማሪው ከመደበኛ የሥራ ሰዓት በተጨማሪ በበሮ፣ በላቦራቶሪና በመሳሰሉት ቦታዎች በቅርብ በመገኘት የምርምር ሥራውን እንዲሰራ ለማድረግና ለክትትል እንዲያመቸው፣

- ተማሪሚዎች አንድ ቦታ በመኖራቸው ያላቸውን እወቀትና ልምድ እርስ በእርስ ለመለዋወጥ የተሻለ ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር፣
- በአንዳንድ የምርምር ሜከላት አካባቢ ካለው ተጨባጭ ነባራዊ ሁኔታ ተማሪሚዎችን ሊያኖር የሚያስችል የተሟላ የከራይ ቤት በቅርበት ባለመኖሩ፣
- በምርምሩ ሥራ ላይ ችግር ቢያጋጥም በቅርብ በማግኘት መፍትሔለመስጠት ስለሚያዳ፣
- በሥራ ባህሪያቸው ምክንያት በቅርበት እንዲገኙ የሚፈለጉ ሠራተኞች ከመደበኛ የሥራ ሰዓታቸው ውጭለሚሰሩ ሥራዎች ሞራዊ ድጋፍ መስጠት እንዲቻሉ፣
- ከሥራቸው ባህሪ የተነሳ በቅርብ በማግኘት ለምርምር ድጋፍ ሰጭ የሆኑ ሠራተኞችን ለማበረታታትና ለማትጋት፣

በአጠቃላይ ለምርምሩ ስኬታማነትና ውጤታማነት ሰብል መኖሪያ ቤት ባላቸው ሜከላት ለሚቀሩ የኢንስቲትዩቱ ተማሪሚዎች ከመደበኛ ስራቸው በተጨማሪ በበሮ፣ በላብራቶሪ በመሳሰሉት ቦታዎች በቅርብ በማኖርት የምርምር ሥራቸውን እንዲሰራ ለማድረግ ለከትትል እንዲያመቻ እንዲሁም በሥራ አስፈላጊነት በቅርብ ተገኝተው ለምርምር ሥራው ድጋፍ ለሚሰጡ ሌሎች ሠራተኞች የመኖሪያ ቤት አገልግሎት በነጻ መስጠቱ አስፈላጊና ተገቢ መሆኑ ይታመናል፡፡

## 3. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

3.1 <u>ኢንስቲትዩቱ ማለት፡-</u> በአዋጅ ቁጥር 79/1989 የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ድርጅትን ለማቋቋም የወጣውን በማሻሻል 79/8925 የአስፈጻሚ አካላት ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በአዋጅ ቁጥር 471/98 በወጣው መሠረት የተቋቋመው የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ማለት ነው፡፡

3.2 <u>ሜከል ማለት፡-</u> በኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ስር በየትኛውም ደረጃ የሚገኙ የኢንስቲትዩቱ ቅርንጫፍ የግብርና ምርምር ሜከላት ናቸው፡፡

3.3 <u>የኢንስቲትዩቱ መኖሪያ ቤቶች ማለት፡-</u> በዚህ መመሪያ ላይ በተገለፀው መሠረት ለተማሪሚዎች/ሌሎች ሞተኞች በሥራ ባህሪያቸው ምክንያት ተከራይተውበሥራ አስፈላጊነት ነጻ እንዲኖሩበት ኢንስቲትዩቱ ያሰራቸው፣ ወይንም ከከራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት የተከራያቸው፣ ወይንም ከሌሎች ተቋማት ጋር በመስማማት የተረከባቸው መኖሪያ ቤቶች ማለት ነው፡፡

3.4 <u>ለግል የሚሰጥ መኖሪያ ቤት ማለት፡-</u> አንድ ተመራማሪ ወይም የማቤቱ ሠራተኛ ከቤተሰቦቹ ጋር ለመኖር የሚያስችል ለትዳርና ህጋዊ ልጆች ካሉት እነዚህን የቤተሰብ ቁጥር ብዛትን ከግምት ውስጥ በማስገባት በማቤቱ ቅጥር ውስጥ ወይንም ውጭ የሚገኝና በማቤቱ የተገነባ ወይንም ማቤቱ ከከራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት የተከራየው ወይንም በሌላ ሚልኩ ከሌላ ተመሳሳይ ተቋም ጋር ባለው ግንኙነት በስምምነት የተረከበው መኖሪያ ቤት ቤተሰቡን ይዞ እንዲኖርበት የተከራየው ወይም በሥራ አስፈላጊነት በነጻ እንዲኖርበት የተፈቀደለት ቤት ማለት ነው፡፡

3.5 <u>በጋራ የሚሰጥ መኖሪያ ቤት ማለት፡-</u> በሁኔታዎች አስገዳጅነት/አስፈላጊነት ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ተመሳሳይ ፆታ ያላቸው ተመራማሪዎች/ሌሎች ሠራተኞች በማቤቱ ውስጥ የሚገኘውን መኖሪያ ቤት በጋራ እንዲኖሩበት በሥራ አስፈላጊነት እንዲኖሩበት የተፈቀደላቸው መኖሪያ ቤት ማለት ነው፡፡

3.6 <u>የመኖሪያ ቤት ደረጃ ማለት፡-</u> በኢንስቲትዩቱ የተሰሩ/የሚሰሩ መኖሪያ ቤቶች በሚኖራቸው የመኝታ ክፍሎች ብዛትን ምክንያት በማድረግ የሚሰጥ ደረጃ ነው፡፡ በዚህ መሠረት ባለ ሦስት መኝታ ቤት ደረጃ 1፣ ባለ ሁለት መኝታ ቤት ደረጃ 2፣ ባለ አንድ መኝታ ቤት ደረጃ 3፣ ባለ አንድ ክፍልና የጋራ ሳሎንና ኩሽና ደረጃ 4 እንዲሁም ባለ አንድ ክፍል ብቻ ደረጃ 5 ማለት ነው፡፡

3.7 <u>የቤት ማልገያ ዕቃ ማለት፡-</u> በተቋማቱሚከሉ መኖሪያ ቤት እንዲኖሩበት የተከራዩት ወይም በሥራ አስፈላጊነት በነጻ እንዲኖሩበት የተፈቀደላቸው ሠራተኞች እንዲገለገሉባቸው የሚሰጣቸው የቤት ቁሳቁሶች ማለት ነው፡፡

3.8 <u>ሠራተኛ ማለት፡-</u> በኢንስቲትዩቱ በቋሚነት ወይም በኮንትራት ውል ስምምነት የተቀጠረ ሠራተኛ ማለት ነው፡፡

3.9 <u>ቤተሰብ ማለት፡-</u> የኢንስቲትዩቱን መኖሪያ ቤት የተከራዩ ወይም በሥራ አስፈላጊነት በነጻ እንዲኖሩበት የተፈቀደላቸው ሠራተኞች ባል/ሚስት/ልጅ/ልጆች እና በቤተሰብ ሕጉ መሠረት በእነርሱ ስር የሚተዳደሩ የቅርብ ዘመዶች ማለት ነው፡፡

3.10 <u>የቤተሰብ ብዛት ማለት፡-</u> የሠራተኛው ባለቤትና ህጋዊ ልጆቻቸውን ወይም በቤተሰብ ሕጉ መሠረት በስራቸው የሚተዳደሩ ሰዎች ብዛት ማለት ነው፡፡

3.11 <u>የማዕከል የመኖሪያ ቤት ድልድል ኮሚቴ ማለት፡-</u> የማዕከል የመኖሪያ ቤት ድልድል/ሽግሽግ የሚሠራና የመኖሪያ ቤት አጠቃቀምን በተመለከተ የማዕከሉን ዳይሬክተር የሚያማክር ኮሚቴ ማለት ነው፡፡

3.12 <u>የረዥም ጊዜ ስልጠና ማለት፡-</u> የትምህርት ደረጃ ለውጥ የሚያስገኝ ከ6 ወር በላይ የሆነ ስልጠና ማለት ሲሆን የሳንዱች ስልጠናንም ያካትታል፡፡

3.13 <u>የአጭር ጊዜ ሥልጠና ማለት፡-</u> የትምህርት ደረጃ ለውጥ የማያስገኝ 6 ወርና ከዚያ በታች የሚቆይ ስልጠና ማለት ነው፡፡

3.14 <u>የጋራ የቤት የማብሰያ ዕቃዎች ማለት፡-</u> በጋራ ቤት የተከራዩ ወይም በሥራ አስፈላጊነት በነጻ እንዲኖሩበት የተፈቀደላቸው ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሠራተኞች በጋራ የሚገለገሉባቸው የቤት ውስጥ ቁሳቁሶች ማለት ነው፡፡

3.15 <u>የመኖሪያ ቤት ተጠቃሚ ማለት፡-</u> በዚህ ካየሥራ ሚዎች፣ ተመራማሪዎችና ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች የመኖሪያ ቤት አገልግሎት አሰጣጥና አጠቃቀም የአፈጻጸም መመሪያ መሠረት መኖሪያ ቤቱን የመጠቀም መብት ያገኘ የኢንስቲትዩቱ/የማዕከሉ ሠራተኛ ማለት ነው፡፡

3.16 <u>የአገልግሎት ዘመን ማለት፡-</u> በመኖሪያ ቤት ድልድልና ሽግሽግ የሚያገለግል በኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ውስጥ በተመራማሪነት ወይም በሌላ ደረጃ ከተቀጠረበት/ከተመደበበት ቀን ጀምሮ እስከ ቤት ድልድሉ ቀን ድረስ የሚቆጠር የአገልግሎት ዘመን ማለት ነው፡፡

## 4. የመኖሪያ ቤት ድልድል መመዘኛ መስፈርቶች

4.1 የሥራ ደረጃ
4.2 የሠራተኛው የሥራ ባህሪ /በማዕከል መኖር አስፈላጊነት/
4.3 የቤተሰብ ብዛት
4.4 የአገልግሎት ዘመን
4.5 የሥራ ኃላፊነት

## 5. የመኖሪያ ቤት ድልድል/ሽግሽግ አፈጻጸም ቅደም ተከተል

5.1 በሥራ ባህሪ ወይም በሜከል የመኖር አስፈላጊነት /ያለወደደር የሚሰጥ/

5.2 ለሠራተኛው በወደደር የሚሰጥ የነጥብ ማጠን

5.3 የሠራተኛው ፆታ ወይንም በማግሥት መሜያ መሠረት ብልጫ ነጥብ የሚሰጣቸው (⁻ሶሶስቌቂ፫ቓሽባስ ⁻ሰቓሽቌቓ)

5.4 በሜከል አገልግሎት ከሚሰጡ መኖሪያ ቤቶች ወስጥ 70 ኀ ለተሚምሜ ለቴክኒክ ድጋፍ ሰጭና

ለአስተዳደር ድጋፍ ሰጭ ሰራተኞች 30 ኀ ሆኖ አፈፃጸፀሙ በተመለከተ በወጣታቸው ቅደም ተከተል መሰረት ለተጠቀሱት ሰራተኞች ይደለደላል ፡፡

## 6. በሥራ ባህሪ ምክንያት መኖሪያ ቤት ያለ ወደደር የሚፈቀደላቸው ሠራተኞች

### 6.1 በሜከሉ ደረጃ ባሉት የተሻሉ መኖሪያ ቤቶች ወስጥ ያለ ወደደር እንዲኖሩ የተፈቀደላቸው

6.1.1 የሜከል ዳይሬክተር

6.1.2 በሜከል የተመደበ የሥራ ሂደት ዳይሬክተር

6.1.3 ሜሮ ተሚምሜ (ከአንድ በላይ ሆነው ካመለከቱ እርስ በርሳቸው የሚወዳደሩ ይሆናል)

6.1.4 በስምምነት የሚቀጠሩ ከፍተኛ ባለሞያዎች

6.1.5 ተቋሙ በልዩ ሁኔታ በሜከሉ የሚመደባቸው የምርምር ፕሮጀክት የወጭ ኤክስፐርቶች

6.1.6 የሰው ሀብት ሥራ አመራርና ልማት የሥራ ሂደት ተጠሪ

6.1.7 የግዥ ፋይናንስ ንብረት ሜጀመንት የሥራ ሂደት ተጠሪ

### 6.2. እንደሜከሉ ሁኔታ በሜከሉ ወስጥ ባሉ በደረጃ 3 እና በታች ቤቶች ወስጥ ያለ ወደደር እንዲኖሩ

### የተፈቀደላቸው

6.2.1 አንድ የእንስሳት ጠና ባለሞያ (እንስሳቶች ባሉበት ሜከል)

፮.፪.፪ አንድ ኤሌክትሪሺያን

፮.፪.3 አንድ ሹፌር

፮.፪.4 የቴክኖለጂ ብዜት አስተባባሪ

፮.፪.5 የሜትሮለጂ ጣቢያ ባለባቸው ማዕከላት የሜትሮለጂ ባለሞያ (ኦቭዘርቨር)

፮.፪.፮ ከፍተኛ የመስኖ ግንባታና ጎርፍ አደጋ ባለባቸው ማዕከላት ላይ የፓምፕ ኦፕሬተር

## ፯. ተመራማሪው ባለሞያው ባለበት ደረጃ ላይ ባሉ ቤቶች ያለ ወድድር እንዲኖሩ የተፈቀደላቸው

፯.1 ቀደም ሲል የነበረበትን የመኖሪያ ቤት በሥራ አስፈላጊነት ያስረከበ ተመራማሪ

፯.፪ በአካል ጉዳት ምክንያት ከሩቅ ተመላልሶ ለመሥራት የማይችል ተመራማሪ/ ሠራተኛ ደረጃው እንደማዕከሉ ተጨባጭሁኔታ በሚወሰነው የመኖሪያ ቤት ያለወድድር ይመደባል

## ፰. ለተመራማሪዎችና ለድጋፍ ሰጭ ሠራተኞች የመኖሪያ ቤት ድልድል/ሽግሽግ መመዘኛ መስፈርቶች የመወዳደሪያ ነጥብ አሰጣጥ

፰.1. ወድድሩ የሚካሄደው ተመራማሪው ከተመራማሪ እንዲሁም ድጋፍ ሰጪው ከድጋፍ ሰጪው ጋር ነው፡፡ እንደምርምር ማዕከሉ ተጨባጭሁኔታ ያሉትን ቤቶች ለተመራማሪዎችና ድጋፍ ሰጪዎች የመለየቱ ሥራ የማዕከሉ ማኔጅመንት ይሆናል፡፡

## ሠንጠረዥ 1. ለተመራማሪዎች የሥራ ደረጃና የሀላፊነት ቦታዎች የሚሰጥ አጠቃላይና ዝርዝር ነጥብ

| | |
|---|---|
| **ሀ/ ለሥራ ደረጃ የሚሰጥ አጠቃላይ ነጥብ** | **50ነ** |
| ከፍተኛ ተመራማሪ | 50ነ |
| ተመራማሪ ህህ | 45ነ |
| ተመራማሪ ህ | 40ነ |
| ተባባሪ ተመራማሪ ህህ | 35ነ |
| ተባባሪ ተመራማሪ ህ | 30ነ |
| ረዳት ተመራማሪ ህህ | 25ነ |
| ረዳት ተመራማሪ ህ | 20ነ |
| ጀማሪ ተመራማሪ | 15ነ |
| **ለ/ ለሀላፊነት ቦታ የሚሰጥ አጠቃላይ ነጥብ** | **20ነ** |
| የኬዝ ቲም አስተባባሪ (በብሔራዊ ደረጃ) | 20ነ |
| የሥራ ሂደት ተጠሪ | 15ነ |
| የኮሚቴ አስተባባሪ (በብሔራዊ ደረጃ) | 10ነ |
| **ሐ/ ለአገልግሎት ዘመን የሚሰጥ አጠቃላይ ነጥብ** | **15ነ** |
| ከ12 ዓመት በላይ | 15ነ |
| ከ8 ዓመት እስከ 11 ዓመት | 12ነ |
| ከ4 ዓመት እስከ 7 ዓመት | 8ነ |
| ከተቀጠረበት ቀን እስከ 3 ዓመት | 4ነ |
| **መ/ ለቤተሰብ ብዛት የሚሰጥ አጠቃላይ ነጥብ** | **15ነ** |
| የልጆች ብዛት ከ2 በላይ | 15ነ |
| የልጆች ብዛት ከ1-2 | 10ነ |
| ለባለትዳር | 5ነ |

ሠንጠረዥ ፪. ለድጋፍ ሰጭሠራተኞች የሥራ ደረጃና የኃላፊነት ቦታዎች የሚሰጥ አጠቃላይና ዝርዝር ነጥብ

| | |
|---|---|
| ሀ/ ለድጋፍ ሰጭሠራተኞች የኃላፊነት ቦታ የሚሰጥ አጠቃላይ ነጥብ | 70ነ |
| የሥራ ሂደት ተጠሪ | 70ነ |
| የኬዝ ቲም አስተባባሪ | 60ነ |
| ኦፊሰሮች (ክፍል ኃላፊዎች) | 50ነ |
| ባለሙያዎች | 40ነ |
| ሠራተኞች | 30ነ |
| ለ/ ለአገልግሎት ዘመን የሚሰጥ አጠቃላይ ነጥብ | 15ነ |
| ከ1፪ ዓመት በላይ | 15ነ |
| ከ፰ ዓመት እስከ 11 ዓመት | 1፪ነ |
| ከ4 ዓመት እስከ ፯ ዓመት | ፰ነ |
| ከቀተጠረበት ቀን እስከ ፫ ዓመት | 4ነ |
| ሐ/ ለቤተሰብ ብዛት የሚሰጥ አጠቃላይ ነጥብ | 15ነ |
| የልጆች ብዛት ከ፪ በላይ | 15ነ |
| የልጆች ብዛት ከ1-፪ | 10ነ |
| ለባለትዳር | 5ነ |

፰.፪ ለወድድር የቀረቡ ሠራተኞች ነጥብ ደምር እኩል ከሆነ ለሴት ተወዳዳሪ ቅድሚያ ይሰጣል፡፡ ተወዳዳሪዎች ወንዶች ወይም ሴቶች ከሆኑ ከፍተኛ የሥራ ደረጃና ቀጥሎ በቤተሰብ ብዛት ቅድሚያ ይሰጣል፡፡

፰.፫ ለወድድር የቀረቡ ሠራተኞች ነጥብ ደምር እኩል ከሆነ የመኖሪያ ቤት ደልደል ተወዳዳሪዎች ወይም ተወካይ በተገኙበት በሚወጣ ዕጣ ይሆናል፡፡

## ፱. የኢንስቲትዩቱ መኖሪያ ቤትና ማልገያ ዕቃዎች ድልደል/ሽግሽግ የሚከተባበር ኃላፊነት

9.1 የግ/ፋ/ን/ማ ዳይሬክቶሬት የዚህ መመሪያ አስፈጻሚሆኖ የማስተባበሩን የሥራ ድርሻ ይወጣል፡ ፡

በመሆኑም -

9.2 ይህንን መመሪያ ተግባር ላይ ያውላል፣ ከዚህ ውጭከሜከላት የሚቀርቡ ጉዳዮችን አሰባስቦና ተገቢውን የማሻሻያ ጥናት አከናውኖ ለተቋሙምክትል ዋና ዳይሬክተር ያቀርባል፣ ይከታተላል፣ ውሳኔ ያሰጣል፡ ፡

9.3. በመመሪያው አፈጻጸም ላይ ከሚሄዩ ችግሮች በመነሳት የሚሰጡ አስተያየቶችን ከተጠቃሚዎች ወይም ምርምር ሜከላት አሰባስቦ መመሪያው የሚሻሻልበትን መንገድ አጥንቶ ለተቋሙ ምክትል ዋና ዳይሬክተር ያቀርባል፡ ፡

## 10. የሜከል የመኖሪያ ቤት ደልደል/ሽግሽግ ኮሚቴ ተጠሪነትና ኃላፊነት

10.1 የመኖሪያ ቤት ደልደል/ሽግሽግ ኮሚቴ በግብርና ምርምር ሜከል ይቋቋማል፡ ፡

10.2 ተጠሪነቱ ለሜከሉ ዳይሬክተር ይሆናል፡ ፡

10.3 የኮሚቴው የአገልግሎት ዘመን ሁለት ዓመት ነው፡

10.4 በመመሪያው መሠረት የመኖሪያ ቤት ደልደልና ሽግሽግን ያደርጋል፡ ፡

10.5 የመኖሪያ ቤት ደንብ ለማሻሻል እንዲቻል ለሜከል ዳይሬክተር የማሻሻያ ሃሳብ ያቀርባል፡ ፡ እንደሜከሉ ነባራዊ ሁኔታ ይህንን ገዥ የተቋም መመሪያ በሚጥስ መልኩ ተቋሙ እያስፈቀዱ አነስተኛ ማሻሻያዎች እየተጠና ተግባር ላይ እንዲውል ይደረጋል፣ ይህም በተቋም አመራር ሙሉ ፈቃድ ይፈፀማል፡ ፡ በመኖሪያ ቤቶቹ ላይ ጥናት እያደረገ ማሻሻያዎችን ያደርጋል፡ ፡

10.6 የመኖሪያ ቤትና የማልገያ ዕቃዎችን አጠቃቀምና አያያዝን በተመለከተ ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ የቤቶቹን አጠቃላይ ይዘት በማየት የማስተካከያ ሃሳብ ለሜከል ዳይሬክተር ማቅረብ አለበት፡ ፡

## 11. በሜከላት የኮሚቴ አባላት ዝርዝር

11.1 የግ/ፋ/ን/ማ ተጠሪ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . ሰብሳቢ

11.2 የሰው ኃብት ሥራ አመራርና ልማት የ/ሥሚ ተጠሪ . . . . . . . . . . . . . . .

ፀሐፊ

11.3 በተማሪሚዎች የሚዊጥ z ተማሪሚ እና የሥሮዓተ ፆታ ተወካይ . . .

አባል ይሆናሉ፡ ፡

12. የመኖሪያ ቤትና የቤት ማልገያ ዕቃዎች ደልደሏ/ሽግሽግ አፈጻጸም፡ አያያእና አጠቃቀም

12.1 ኢንስቲትዩቱ በየሜከላቱ ባሉት የመኖሪያ ቤቶች ለሥራው አስፈላጊነት ሲባል በወጣው መመዘኛ መሠረት ለሠራተኞቹ የመኖሪያ ቤትና የቤት ማልገያ ዕቃዎችን እንደአስፈላጊነቱ ቢያከራይምበሰጥም ይህንን ማግኘቱ ግን እንደ ግዴታ ሊወሰድ አይገባም፡ ፡

12.2 በዚህ መሜያ መሠረት በሥራ ባህሪያቸው ምክንያት መኖሪያ ቤት ያለወደደር በቀጥታ ከሚከራይላቸው/ከሚቀደላቸው የኢንስቲትዩቱ ሠራተኞች በስተቀር ሌለው ሠራተኛ በተቀመጠው መስፈርት መሠረት ተወዳድሮ ተማሪሚ ከሆነ በከራይ/ሌለ ሠራተኛ ከሆነ ደግሞ በነጻ ቤት ያገኛል፡ ፡

12.3 ከሜከል ወደ ሜከል በሚደረግ ዝውውር በኢንስቲትዩቱ/በሜከሉ ቤት ተከራይተው/ተሰጥቷቸው የነበሩ ሠራተኞች ቤት ሊያገኙ የሚችሉት በመሜያው መሠረት ተራቸውን ጠብቀው ይሆናል፡ ፡

12.4 ባለትዳሮችና የቤተሰብ ኃላፊዎች ስለቤተሰባቸው ህጋዊ ማስረጃ እንዲያቀርቡ ሲጠየቁ ማቅረብ አለባቸው፡ ፡ ከቤተሰብ ጋር መኖር የሚቻለው ለቤተሰብ በተፈቀደ መኖሪያ ቤቶች ብቻ ነው፡ ፡ ሠራተኛው አብረውት የሚኖሩት ቤተሰቦችና የግል እንግዶች ለሚፈጥሩት ችግር ተጠያቂ ነው፡ ፡

12.5 ባለትዳሮችና የቤተሰብ ኃላፊዎች እንደ አስፈላጊነቱ በግል ወይም በጋራ መኖሪያ ቤቶች ሊደለደሉ/ሊሸጋሸጉ ይችላሉ፡ ፡

12.6 በየሜከሉ የሚገኙ መኖሪያ ቤቶች ውስጥ እንደየቤቶቹ ሚጠን ማያዝ የሚገባቸው ከፍተኛው የሰው ብዛት በየሜከላቱ የሚገኙ የመኖሪያ ቤት ደልደሏ/ሽግሽግ ኮሚቴ አማካኝነት የሚወሰን ይሆናል፡ ፡

12.7 አጠቃላይ የማዕከሉን የመኖሪያ ሰፈርና አካባቢ ወፅትና ፅዳት በተመለከተ ስራው የማዕከሉ ጠቅላላ አገልግሎት ኃላፊነት ይሆናል፡፡ በሆነም እያንዳንዱ ሰራተኛ ለተረጀበው ቤትና የአካባቢ ጸዳት ኃላፊነት አለበት፡፡

12.8 ኢንስቲትዩቱ መኖሪያ ቤቱን ለአስቸኳይ ሥራ ከፈለገው የአንድ ወር ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶ ሠራተኛው የተረከበውን ቤት ያስረክባል፡፡ ሆኖም ግን ሠራተኛው በዚህ መመሪያ በተመለከተው መሠረት በድጋሚ መወዳደር ሳያስፈልገው ተመሳሳይ ቤት በቅድሚያ ያገኛል፡፡

12.9 ሠራተኛው የተረከበውን መኖሪያ ቤትና የመኖሪያ ቤት ማልገያ ዕቃዎች እንዲያስረክብ በተጻፈለት ጊዜ ውስጥ ካላስረከበ ቤቱ በኮሚቴ ታሽጎ አስፈላጊው እርምጃ ይወሰዳል፡፡

12.10 ከሠራተኛው/ዋ አቅምቁጥጥር በላይ ለሆኑ የንብረት ጉዳቶችና ብልሽቶች ኢንስቲትዩቱ/ማዕከሉ ተገቢውን ጥገና ያደርጋል፡፡

12.11 ለሾፌር የሚሰጥ ቤትን በተመለከተ ሥራው በዙር ተራ የሚከናወን ስለሆነ የቤተሰብ መኖሪያ ቤት ያልሆነ ለማደሪያነት ብቻ የሚያገለግል አንድ ክፍል ቤት ይፈቀዳል፡፡

12.12 ያለ ውድድር ለአንድ የእንስሳት ጤና ባለሙያ የሚሰጥ መኖሪያ ቤትን በተመለከተ በማዕከሉ ውስጥ የእንስሳት ምርምር የሚካሄድበትና እንስሳቶች የሚኖሩበት ዘርፍ ሲኖር ብቻ ነው፡፡

12.13 ለሠራተኞች ማዘናኛ ክበብ ሥራ አስኪያጅ/አስተባባሪ ከሥራ ሰዓት ውጭ ጭምር አገልግሎት የሚሰጥ በመሆኑ ለማደሪያ የሚሆን አንድ ክፍል ቤት ይፈቀድለታል/ላታል፡፡ ሆኖም በሚሰጠው መኖሪያ ቤት ላይ ለሚደርሰው ጉዳት ለመጠየቅ እንዲያስችል በቅጥር ውሉ ውስጥ ወይም ቤቱ ሲሰጠው በቂ ዋስትና እንዲያሲዝ ይደረጋል፡፡

12.14 የመኖሪያ ቤት ከባድ ጥገናን በተመለከተ ኢንስቲትዩቱና ማዕከላት ከሚመለከታቸው ባለሙያዎች ጋር በመሆን በየአምስት ዓመቱ የሚያደስበትን ሁኔታ ያመቻቻሉ፡፡

12.15 አነስተኛ ጥገናዎችን በተመለከተ ማዕከላት በጀት በማስያዝ የሚፈልጉትን ዕቃዎች አሟልተው ጥገናው እንዲከናወን ያደርጋሉ፡፡

12.16 በኢንስቲትዩቱ ፍላጎት መሠረት መደበኛ ባልሆነ ሥራ ለአጭር/ረጅም ጊዜ ሥራ ወደ ዋናው መቤት ወይም ወደ ሌላ የሚሄድ/የምትሄድ ሠራተኛ የነበረበት/ችበት ሜከል መኖሪያ ቤትን እንደ ያዘው/ያዘች መቆየት የሚችለው የምትችለው የሄደበት/ የተላከበት ጉዳይ እስከሚጠናቀቅ ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ ብቻ ይሆናል፡፡ ይቆያል፡፡

12.17 ለባለትዳር ሠራተኞች በባል ወይም በሚስት አማካይነት በሚያገኙት ዕድል የሚጠቀሙበትን ጊዜ የተሻለውን ቤት አንደኛውን ብቻ ለተመራማሪዎች በኪራይ ለሌሎች ሠራተኞች በነጻ እንዲያገኙ ይደርጋል ፡፡

## 13. የመኖሪያ ቤትና የቤት ማልገያ ዕቃዎችን በተመለከተ የሠራተኞች ግዴታ

13.1 መኖሪያ ቤት የተሰጣቸው ነዋሪዎች በግልም ሆነ በጋራ የተጠቀሙትን የስልክ፣ የመብራትና ውሃ ክፍያ ሂሳብ የመክፈል ግዴታ አለባቸው፡ ለዚህም አፈጻጸም ተቋሙ ውጥ አሠራር የሚዘረጋ ይሆናል፡፡

13.2 መኖሪያ ቤትን ማልገል የሚቻለው ለመኖሪያ ቤት በተዘጋጀው ውልና የሚካከቢያ ሰነድ ላይ ተገልጋዩ/ዋ ፈርሞማ ሲቀበል/ስትቀበል ብቻ ነው፡

13.3 በማናቸውም ምክንያት ያለበትን ሜከል የሚለቅ ሠራተኛ የመኖሪያ ቤትና የቤት ዕቃዎች ማስረከቡ በንብረት ክፍል ሳይረጋገጥ ሜልቀቂያ/ስንብት አይሰጠውም፡

13.4 ሠራተኛው እንዲኖርበት በተከራየው/በተፈቀደለት መኖሪያ ቤት ወይም ሰርቪስ ቤቶች ውስጥ መኖር የሚችለው በጽሁፍ ያስመዘገባቸውን ቤተሰቦቹን ብቻ ነው፡

13.5 ማንኛውም የኢንስቲትዩቱ ሠራተኛ እንዲኖርበት የተከራየውን/የተፈቀደለትን መኖሪያ ቤት ከሌላ ሠራተኛ ጋር በራሱ ፈቃድ መለዋወጥ፣ መከፋፈል፣ ማፍረስ፣ ከባድ እድሳትም ሆነ ጥገና ማድረግ እንዲሁም ከመኖሪያነት ውጭ ለሌላ አገልግሎት ማዋል አይፈቀድም፡

13.6 ማንኛውም ሠራተኛ ከኢንስቲትዩቱ/ሜከሉ እውቅና ውጭ የተሰጠውን መኖሪያ ቤት ያለበቂ ማስረጃ ከሁለት ወር በላይ ቆልፎ ከተገኘ ማቤቱ በኮሚቴ ቤቱን ተረክቦ አገልግሎት እንዲሰጥ ያደርጋል፡፡

13.7 በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር ለረጅም ጊዜ ሥልጠና የሚሄድ ሠራተኛ በኪራይም ሆነ በነጻ እንዲኖርበት የተረከበውን የመኖሪያ ቤትና ንብረት ከመሄዱ በፊት የማስረከብ ግዴታ አለበት፡፡

13.8 ማንኛውም የኢንስቲትዩት ባልደረባ ለሚኖርበት ቤትና ለግቢው እንዲሁም ለተረከበው ንብረት ተገቢውን ጥንቃቄና እንክብካቤ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡ የመኖሪያ ቤት እና የማልገያ ዕቃ ብልሽት ከጥንቃቄ ጉድለት ሆኖ ሲገኝ በሚመለከተው ባለሙያ ተረጋግጦ በሠራተኛው ኪሳራ የጥገና አገልግሎት የሚደረግ ይሆናል፤ ወጪውን ተከራይ እንዲከፍል ይደረጋል፡፡

13.9 አገልግሎት የሚሰጡም ሆነ የሚሰጡ የመኖሪያ ቤት ማልገያ ዕቃዎች የንብረት ማዘዋወሪያ ቅፅ ሳይሞላ ከአንዱ ቤት ወደ ሌላ ቤት ማዛወር አይቻልም፡፡

13.10 ማንኛውም የኢንስቲትዩት ባልደረባ በመኖሪያ ቤት ወስጥ የሚገለግሉ ንብረቶች በሚኖሩበት ወቅት የማስወገጃ ፎርም ሞልቶ ወደ ንብረት ማኔጅመንት እንዲመልሱ ማድረግ አለበት፡፡

13.11 በማንኛውም ምክንያት መኖሪያ ቤቱን የሚለቅ ሠራተኛ በራሱ ፈቃድ መኖሪያ ቤቱን ለሌላ ሰው ማስተላለፍ አይችልም፡፡

13.12 በራሱ ፈቃድና በጠፈታ ማቤቱን የሚለቅ ሠራተኛ ከአንድ ወር በፊት ቤቱንና የተረከባቸውን ንብረቶች ማስረከብ አለበት፡፡

13.13 ከማቤቱ በሞት የተለየ ባልደረባ ቤተሰቡ እንዳይጉላላ ለተጨማሪ ሦስት ወር ጊዜ ተሰጥቶ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ቤቱና ንብረቱን ቤተሰቡ ያስረክባል፡፡

13.14 በከባድ ህመም ምክንያት ከምድብ የሥራ ቦታው ላይ የተለየ የመኖሪያ ቤት ተጠቃሚ ሠራተኛ በህግ የተፈቀደለትን ፍቃዶች ካጠናቀቀ በኋላ ለተጨማሪ 3 ወራት እንዲቆይ ተደርጐ ከተጠቀሰው ጊዜ በኋላ የተረከበውን ቤትና ንብረት ያስረክባል፡፡

13.15 የመኖሪያ ቤት ማልገያ ቋሚ ዕቃዎች ቆጠራ በየዓመቱ ሲካሄድ ሠራተኛው የተረከበውን ንብረት የማስቆጠር ግዴታ አለበት፡፡

13.16 ሠራተኛው በሚኖርበት መኖሪያ ቤትና በሚለገልባቸው የመኖሪያ ቤት ማልገያ ዕቃዎች ላይ ጥፋት ወይም ብልሽት ቢደርስ ወዲያውኑ ማስወቅ አለበት፡፡ ጥፋቱ የተከሰተው ከጥንቃቄ ጉድለትና አያያዝ ከሆነ ሠራተኛው ለጥፋቱ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

13.17በማረፊያ ጊቢ ውስጥ የቤት እንስሳት ማርባትና ንብ ማርባት አይፈቀደም፡፡ እንዲሁም ባልተፈቀዱ ቦታዎችም እርድ ማድረግ የተከለከለ ነው፡፡

13.18ይህን የማረፊያ ቤት መመሪያ የማያከብርና ደንጋጌዎችን ጥሶ የተገኘ ሠራተኛ ድርጊቱን ለሚፈጽሙ በኢንስቲትዩቱ ወይም በማዕከሉ የድልድል አስተባባሪ በደንብ ሰረጋገጥ በመጀመሪያ በጽሁፍ የሚሰጥ የቃል ማስጠንቀቂያ፣ ቀጥሎ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት የሚደጋገም ከሆነ የማዕከሉ የማረፊያ ቤት ድልድል/ሽግሽግ ኮሚቴ ለማዕከሉ/ለኢንስቲትዩቱ ዳይሬክተር በማሳወቅ በህጋዊ መንገድ ቤቱን እንዲለቅ ይደረጋል፡፡

13.19የተለየ ጥቅም ለማግኘት በማሰብ በትዳር አብረው እየኖሩ ነገር ግን ለማዕከሉ/ኢንስቲትዩቱ ሕጋዊ የጋብቻ ሰርተፊኬት የማያቀርቡ ተመራማሪዎች/ሠራተኞች የቤተሰብ ሕግን መሠረት በማድረግ አስፈላጊው የዲሲፕሊን ቅጣትና ሕጋዊ እርምጃ የሚወሰድባቸው ይሆናል፡፡ ይህንንም የተቋሙ የሕግ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ተከታትሎ ተፈጻሚ ያደርጋል፡፡

13.20ለረዥም ጊዜ ትምህርት የሚሄድ ተመራማሪ የሚኖርበትን ቤት ማስረከብ ይኖርበታል፣ መንግሥት የፈቀደውም የማረፊያ ቤት አበል ትምህርቱን አጠናቅቆ እስከሚመለስ ድረስ የሚቋረጥ ይሆናል፡፡

## 14. የማረፊያ ቤት አጠያየቅና አሰጣጥ ሂደት

የማረፊያ ቤት ያለወድድር እንዲሰጣቸው በዚህ መመሪያ ላይ የተካተቱት የማቤቱ ሠራተኞች በሚያቀርቡት ማመልከቻ መሠረት የቤት ድልድል ኮሚቴ አባላት ያሉትን ክፍት ቤቶች በማሸጋሸግ እንዲሰጣቸው ያደርጋሉ፡፡

14.1. በማዕከሉ ውስጥ ያሉትን ክፍት ማረፊያ ቤቶች ግልጽ በሆነ ማሳወቂያ ቁጥር በማለየት በፕሮቶኮል በተመዘገበ ማስታወቂያ ለቤት ፈላጊዎች የምዝገባ ጥሪ በቤት ድልድል ኮሚቴው ይወጣል፣

14.2 በተቋሙ የማረፊያ ቤቶች ውስጥ ያለወድድርም ይሁን በወድድር እንዲኖሩ የተወሰነላቸው ሠራተኞች ማስታወቂያው ከወጣበት ቀን ጀምሮ በአምስት ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ መመዝገብ ይኖርባቸዋል፣ (በጽሑፍ በተረጋገጠ ሜዕከሉ ዕወቅና በሰጠው ወኪልና ምዝገባው ሊከናወን ይችላል)

14.3 የቤት ድልድል ኮሚቴው የአመልካቾችን ዝርዝር፣ የሥራ ደረጃ እና በዚህ መመሪያ ውስጥ የተካተቱትን አስፈላጊ ሚኛዎች በማጠናቀር በግልጽነት እንዲወዳደሩ ያደርጋል፣

14.4 ኮሚቴው በማስታወቂያ በወጡት የመኖሪያ ቤቶች ላይ የተመዘገበና በመመሪያው መሠረት የሚባቸውን ተወዳዳሪዎች ዝርዝር በግልጽ በማእከሉ ማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ ለሦስት ተከታታይ ቀናት እንዲታይ ያደርጋል፣

14.5 በተሠራው የቤት ድልደላ ሥራ ላይ የሚቀርብ ቅሬታ ካለ ለደልደል ኮሚቴው በጽሑፍ ሚሸው በማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት ተከታታይ ሦስት የሥራ ቀናት ውስጥ መቅረብ ይኖርባቸዋል፣

14.6 የቤት ድልደል ኮሚቴው ጉዳዮችን መርምሮ ከጨረሰ በኋላ ዝርዝር አፈጻጸሙን በሚመለከት ማገደና የሚወዳደሪያ ሠንጠረዡን በማከተት ተፈራርሞ እንዲጸደቅ ለማእከሉ ዳይሬክተር ያቀርባል፣

14.7 የቀረበው የቤት ደልደል ቃለጉባዔ በማእከሉ ዳይሬክተር በከል ይጸድቃል፣

14.8 በወሳኔው መሠረት ቤቱ የተመደበለት/ላቸው ሠራተኛ/ኞች በዚህ መመሪያ ውስጥ በዕዝልነት በተካተተው

ቅጽ አማካይነት ውል ይፈራረማሉ፣

14.9 የውል ስምምነቱን መሠረት ባደረገ መልኩ ለሠራተኛው የተመደበውን የመኖሪያ ቤት እንዲረከብ የጊዜ ፕሮቶኮል ማዘገብ የያዘ ደብዳቤ ይሰጣል፣ በዚህ መሠረትም በኪራይ የተሰጠ ከሆነ በየወሩ በተመኑ መሠረት እንዲከፍል ይደረጋል፡፡

## 15. ለመኖሪያ ቤት ጥገና ፤እድሳት በሚመለከት

15.1 ለመኖሪያ ቤት ጥገና፤ እደሳት ለመኖሪያ ቤት ከሚከፈለው ጥቅማ ጥቅም በቤቶቹ ደረጃ ተቀናሽ ሆኖ ጥገና እደሳት የሚያስፈልጋቸው ቤቶች ተለይተው ለእደሳት አገልግሎት ይውላል ፡፡

15.2 ኢንስቲትዩቱ ከኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት የተከራያቸው፣ ወይንም ከሌሎች ተቋማት ጋር በመስማማት የተረከባቸው መኖሪያ ቤቶች የኪራይ ተመን አከራይ በሚጠይቀው ተመን ይፈፀማል ፡፡

ሠንጠረዥ 3. በኢንስቲትዩቱ የሀሊታ ግብርና ምርምር ማዕከል ተመን በቤት ደረጃ

| የቤት ደረጃ | የኪራይ መጠን |
|---|---|
| ደረጃ 1 | 1500.00 |
| ደረጃ 2 | 1200.00 |
| ደረጃ 3 | 800.00 |
| ደረጃ 4 | 400.00 |
| ደረጃ 5 | 150.00 |

ሠንጠረዥ 4. በኢንስቲትዩቱ የደብረዘይት፣ ሰበታ፣ አምቦ፣ የቁሉምሳ፣ አደአ በርጋ፣ የወንዶገነት፣ የአዋዳ፣ የጫጮ ግብርና ምርምር ማዕከላት ተመን በቤት ደረጃ

| የቤት ደረጃ | የኪራይ መጠን |
|---|---|
| ደረጃ 1 | 1500.00 |
| ደረጃ 2 | 1200.00 |
| ደረጃ 3 | 700.00 |
| ደረጃ 4 | 300.00 |
| ደረጃ 5 | 150.00 |

ሠንጠረዥ 5. በኢንስቲትዩቱ የጅማ፣ የሚዛን፣ የባኮ ግብርና ምርምር ማዕከላት ተመን በቤት ደረጃ

| የቤት ደረጃ | የኪራይ መጠን |
|---|---|
| ደረጃ 1 | 1000.00 |
| ደረጃ 2 | 600.00 |
| ደረጃ 3 | 400.00 |
| ደረጃ 4 | 200.00 |
| ደረጃ 5 | 100.00 |

ሠንጠረዥ 6. በኢንስቲትዩቱ የወረር፣ የፓዌ፣ የአሶሳ፣ የቴፒ፣ የጌራ፣ ሐሩ ግብርና ምርምር ማዕከላት ተመን በቤት ደረጃ

| የቤት ደረጃ | የኪራይ ማጠን |
|---|---|
| ደረጃ 1 | 500.00 |
| ደረጃ 2 | 200.00 |
| ደረጃ 3 | 150.00 |
| ደረጃ 4 | 100.00 |
| ደረጃ 5 | 50.00 |

## 16. ልዩ ልዩ

የመኖሪያ ቤት ላላገኙ ተመራማሪዎች ማገልገል ለሥራ ሚዎች፣ ተመራማሪዎችና የቴክኒክ ረዳቶች ባወጣው መመሪያ መሠረት የተፈቀደላቸው የቤት አበል ይከፈላቸዋል፡፡

## 17. የመመሪያው ተፈጻሚነት

ይህ መመሪያ የሠራተኛ መኖሪያ ቤት በተገነባባቸውና ከማገልገል ተረክቦ በሚያስተዳድራቸው በኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ስር በሚተዳደሩ ማዕከሎችም የምርምር ማዕከላትና ማስተኛ ማዕከላት ሁሉ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## 18. መመሪያውን ስለማሻሻል

መመሪያው እንደ አስፈላጊነቱና እንደ ጊዜው ሁኔታ ሊሻሻል ይችላል፡፡

## 19. የተሻሩ መመሪያዎች

ቀደም ሲል ከነሐሴ 2004 ዓ.ም ጀምሮ በሥራ ላይ የነበረው ካየመኖሪያ ቤትና ማልገያ ዕቃዎች ደልደልና አጠቃቀም መመሪያካ በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡

## 20. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ወይም ምዋና ዳይሬክተር ከፍተኛ ሥራ አመራር ከጸደቀበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አባሪ 1.

# በኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት

## የ________________ምርምር ማዕከል

*የመኖሪያ ቤት ማገልገያ ዕቃዎች ማስተላለፊያ ቅጽ*

**ቓኻሽቒቅሽርቓ ህቓቋቓሽቓበቓስ ቒሶ ሽቒሽሰበቒቓበቒርቒ ሎስቋስርቒሰኻ**
**------------------------- ሽቒሽሰበቒቓበቒርቒ ሎስቋስርቒሰኻ ስቓቓስቒ**
**ሎስቋሽሳስቓቓሽርቒ ሃቒበቋስቋ ሓቒቒቅስቒቓኽ ማቒርቓቋሶስቒ ቒቒቂ**

ቒቒቂ ______ ማቒ

________________________________________

ብሽቒሳሽቓሽ _________________________ ብሽቒሳሽቓሽ ______________________________

ሠስሰቓሽቒቓ _________________________ ሠስሰቓሽቒቓ ______________________________

ሎቒቒቂ ሐቒ. __________________________ ሎቒቒቂ ሐቒ. ____________________________

ርቓስ ______________________________________ ርቓስ

________________________________________

| ሐቒ. | ህቓባስቓቓቒቒኽ ሐቒ. | ሐርቂስ/ ስቋስቒሽቅቓሽቒቓ | ምቓሽቓ | ሕቓኽ. | ምቓሽቓ ቅቒሽሰስ (ሽቒቒ) | ሎስቂርቒቀ |
|---|---|---|---|---|---|---|

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |

ያስረ በው ስም________________________

ፊርማ________________________

የተረ በው ስም________________________

ፊርማ________________________

አባሪ ፪.

## በኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት
## የ________________ምርምር ማዕከል
## የማረፊያ ቤት ውስጥ እንዲኖሩ የተመዘገቡ የቤተሰቦች ዝርዝር

የሠራተኛው ስም________________________

እንዲኖርበት የተሰጠው የማረፊያ ቤት መለያ ቁጥር________________________

የማረፊያ ቤቱን የተረከበበት ቀን____________________

በማረፊያ ቤቱ ውስጥ እንዲያኖራቸው ያስመዘገባቸው ቤተሰቦች ዝርዝር (ከአንድ ወር በላይ በማረፊያ ቤት ውስጥ የሚኖሩ ቤተሰቦች መመዝገብ ይኖርባቸዋል)፡፡

| ተ.ቁ | የቤተሰብ ስም | ዝምድና | በቤቱ ውስጥ እንዲኖሩ የተፈቀደበት ጊዜ (ከ<br>እስከ ________________.) | የነዋሪው ፊርማ | የሥራው ኃላፊ ፊርማ |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |